# « በወዳጅህ ላይ ክፉ አትስራ እርሱ ተማምኖ ከአንተ ጋር ተቀምጦ ሳለ » (መጽሐፈ ምሳሌ 3፤29)

ከታምራት ታረቀኝ

አቶ ግርማ ከሳ ማንን እንደሚሞግቱ ለምንስ እንደሚሟገቱ የሚያውቁ አይመስልም። በሌሎች የሚሰጡ አስተያየቶችን በቅጡ አንብበው ጭብጡን ተረድተው ሊጽፉ ቀርቶ ከራሳቸው ሀሳብ ጋርም በወጥነት የሚዘልቁ ሳለመሆናቸው አንድ ሁለት ጽሁፎቻቸውን ማየት ብቻ ይበቃል። በቀናት ልዩነት የሚፅፉት ቀርቶ በአንድ ቀን የሚጽፉዋቸው ሳይቀር እርስበርስ የሚቃረኑ ለመሆናቸው ጽሁፎቻቸው ይመስክራሉ።

ምርጫ ቦርድ የአንድነት ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው እንደሆኑ አድርጎ በድረ ገጹ አሰራጨ። የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱ‹ን ናትና ድርጊቱ የተፈጸመው በምርጫ ቦርድም ይሁን በእነ ኢ/ር ግዛቸው ህጋዊ የሚሆንበት መሰረት የለውም ብዬ የፖለቲ‹ ፓርቲዎችን ምዝገባ አዋጅና የአንድነትን መተዳደሪያ ደንብ ጠቅሼ ጻፍኩ። አቶ ግርማ የሰጡትና እየሰጡ ያለው አስተያየት ግን እኔ ‹ነሳሁት ጭብጥ ጋር የማይገናኝ ነው። የተቃውሞአቸው ምክንያትም አልገባኝም። ነገረ ስራቸው ሁሉ «በምኒልክ ዘመን የደነቆረ ምኒልክ ይሙት እንዳለ ይኖራል» ይሉ አይነት ነው። አቶ ግርማ የትናንት መነጽራቸውን አውልቀው በአዲስ መነጽር ጽሁፌን ቢያነቡትና በሚገባ ቢረዱት ስህተት የማይሰለቻቸው ቢሆንም የተሳሳተ ሀሳብ ከመሰንዘር ያድናቸው ነበር።

በጽሁፌ መልእክት ያስተላለፍኩትና ጥያቄ ያቀረብኩት ለሁለት ወገኖች ነው። ለምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችና ለኢ/ር ግዛቸው ቡድን። በምርጫ ቦርድ ኦፊሴላዊ ድረ ገጽ የተሰራጨውን መረጃ አስመልክቶ ድርጊቱን የፈጸመው ወገን ይህን ለማድረግ የሚያበቃ የሕግ መሰረት የለውምና የፈጸመበትን ምክንያት እንዲያስራዳ፣ ስህተት ከሆነም ይህንኑ አምኖ እንዲያርም፣ እጄ የለበትም ከእውቅናዬ ውጪ የተፈጸመ ነው የሚል ወገንም ይህንኑ በመግለጽ ራሱን እንዲያጠራ ነው፤ ጥያቄውም መልእክቱም።

የኢ/ር ግዛቸው ቡድን የእኔ አስተያየት ከመጻፉ በፊት እንደ ጉዳዩ ባለቤትነቱ ሁኔታውን ተከታትሎ ቦርዱ ድርጊቱን ለምን እንደፈጸመ ጠይቆ ተቃውሞውን ማሰማትና እንዲታረም መጠየቅ ነበረበት። ዝምታ አምኖ የመቀበል ወይንም የተባባሪነት ምልክት ነው። እነርሱ ያልደፈሩትን ምርጫ ቦርዱ በማድረጉ የመደሰትም ሊሆን ይችላል። መረጃው ከወጣ በኋላ ፈጥኖ መልስ ለመስጠት ያለመፍቀዳቸውም ስለጉዳዩ ያላቸውን አቋም ለመገንዘብ የሚያስችል ነው። ምርጫ ቦርድም እንዲሁ ምላሽ ለመስጠት አልፈቀደም፤ አልፈጠነም። አቶ ግርማ ግን ጉዳዩን በቅጡ ሳይረዱ «ከጳጳሱ ቄሱ» ሆኑና ለተቃውሞ ፈጠኑ።

ጉዳዩ የገባቸው የጽሁፌ ዓላማና ምክንያት የተረዳቸው ጋዜጠኞች ግን እውነታውን ለአንባቢ ለማቅረብ ከሁለቱም ወገን ምላሽ ለማግኘት ቢጥሩም ሳይሳ‹ላቸው ሰነበተ። ነገር ግን ጥያቄውን በዝምታ ማለፍና ማዳፈን አልተቻለምና ሁለቱም ወገኖች በጠያቂዎች ግፊት በተለባበስ ሁኔታም ቢሆን ዘግይተው ምላሽ ሰጡ። በዚህም የጽሁፉ ዓላማ ተሳክቷል።

በእነ ኢ/ር ግዛቸው በኩል፦

1ኛ-- የወ/ት ብርቱ‹ንን ሊቀመንበርነት አምነዋል፡

2ኛ-- በግልጽም ይሁን በስውር ብርቱ‹ንን ሽሮ ኢ/ር ግዛቸውን ሊቀመንበር የሚል ውሳኔም ሆነ መረጃ ለምርጫ ቦርድ እንዳልሰጡ ገልጸዋል።

በምርጫ ቦርዱም በኩል የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሰራተኛ ናቸው የተባሉ ሰው በሰጡት ምላሽ የተሟላም ባይሆን፦

1ኛ-- ቦርዱ የወ/ት ብርቱ‹ን ሚደቅሳን የአንድነት ፓርቲ ሊቀ መንበርነት አምኗል:
2ኛ-- ኢ/ር ግዛቸውን የአንድነት ሊቀመንበር በማለት በድረ ገጹ ያሰራጨው በስህተት መሆኑን አምኖ አስተከክሎአል::

የጽሁፉ ዓላማ ስህተትን በተጨባጭ ማስረጃ በማሳየት መሳሳቱን ያመነና ለመታረም የፈቀደ እንዲታረም ያልፈቀደ ደግሞ ከነጥፋቱ ተሸፋፍኖ እንዳይኖር ገላልጦ ማሳየትና ያለፈውን ለማረም ወኔ ቢያጥረው ወደፊት ተመሳሳይ ስህተት ለመስራት ድፍረቱ እንዳይኖረው ማድረግ ነበርና ዓላማው ግቡን መትቷል::

አቶ ግርማ ይህ ለምን እንዳንገበገባቸው አልገባኝም:: ኢ/ር ግዛቸው ሊቀመንበር መባላቸው ቀርቶ ምክትል ተብለው መገለጻቸው ለዚህም ምክንያት የሆነው የእኔ ጽሁፍ መሆኑ አበሳጭቷቸው ከሆነ አዝናለሁ:: ከእውነት ጋር ሳይሆን ከሰው ጋር የሚወግኑ ሰዎች እውነት በአሸነፈች ግዜ መጮኸቸው የሽንፈታቸው ውጤት ነውና አይገርመኝም:: ሀሰትን ይዞ ጊዜያዊ ድል ይገኛል: በዘላቂነት አሸናፊ መሆን ግን አይቻልም::

ለነገሩ አቶ ግርማ ከእውነት ጋር የቆሙ ቢሆኑ ኖሮ ወ/ት ብርቱ‹ን በታሰረች ሰሞን የተነገረና የተፈጸመው ቢቀር እንኳ በሁለት ምክንያት ለኢ/ር ግዛቸው ጥብቅና ባልቆሙ ነበር::

1ኛ- ኢ/ር ግዛቸው ሚያዝያ 10/2002 ዓ.ም. በተ‹ሄደው የፓርቲው ልዩ ጉባዔ የተሻሩና አሁን « በሥልጣን» ላይ ያሉት በጉልበት እንዲሁም በምርጫ ቦርድ ድጋፍ በመሆኑ፣

2ኛ- ግንቦት 15/2002 ዓ.ም. የፈጸሙት «አስነዋሪ» ተግባር የፓርቲ መሪ ለመሆን የማያበቃቸው በመሆኑ፣

ስለሆነም ኢ/ር ግዛቸውን መደገፍና ለርሳቸው ጠበቃ ሆኖ መቆም የአንድነትን መጠናከር አለመፈለግ ነው:: የመሪ ጥን‹ሬ የድርጅት ጥን‹ሬ ነው:: አስቦና አመዛዝኖ ሳይናገር በሰዓታት ግዜ ውስጥ ይቅርታ ለመጠየቅ የሚብረከረክ ሰው የሚመራው ፓርቲ የህዝብን ተቀባይነት ሊያገኝ በሰላማዊ ትግሉም ገፍቶ ለድል ሊበቃ አይችልም::

ኢ/ር ግዛቸው ጠያቂ ህሊና ቢኖራቸው ኖሮ ያንን ድርጊት በፈጸሙ ማግስት ራሳቸው የመልቀቂያ ደብዳቤ ማስገባት ነበረባቸው:: ነገር ግን እንደ አቶ ግርማ ከሳ ያሉ አጃቢ ደጋፊና አይዞህ ባይ አሏቸውና ከነውርደታቸው የፓርቲ መሪ ነኝ ለማለት ደፍረዋል፡፡

ምርጫ ቦርድ ከዚህ የተለየ ምን እንዲያደርግ ጠብቃችሁ ነው እንዲህ አይነት ጽሁፍ የምትጽፉት የሚሉ ሰዎች ምን ለማለት እንደፈለጉ ግልጽ አይደለም:: ምንም ያድርግ፣ የፈለገውንም ይበል፣ ምርጫ ቦርድ ማን እንደሆነ ስለሚታወቅ አትናገሩት፤ ስህተቱን አታንሱ፤ ኃላፊነቱን እየተወጣ አንዳልሆነም አትንገሩት፤ እያሉን ይሆን? እነዚህ ወገኖች ዛሬም በደፈናው «ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም» እያልን እንድንጮህ ነው የሚነግሩን? ለአመታት ከተሰማው ከዚህ ጩኸት ይልቅ ማስረጃ ጠቅሰን አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ አንቀጾች አጣቅሰን ያቀረብነው ጥያቄ ቦርዱ የሰራውን ስህተት እንዲያምን ብሎም እንዲያርም ማስቻሉን እያዩ ዛሬም በትናንቱ መንገድ መሄድን ለምን እንደሚመርጡ አልገባንም::

በርግጥ «በየቤቱ ተወያይተን በኮሪደር ላይ ተነጋግረን ነው የሾምናቸው የተባሉትን የዶ/ር ነጋሶንና የአቶ ስዬን «የአንድነት ም/ል ሊቀመንበርነት» የተቀበለና ለሚያዝያ 10/2002 ጉባዔ ውሳኔዎች እውቅና ለመስጠት ዳተኛ የሆነው ምርጫ ቦርድ አንንኳን ሊወቀስ ስሙ ሊነሳ አይገባም ማለታቸው የውለታ ጉዳይ ይሆናል፤ለነገም የአደራ መልእክት ያዘለ::

እኛ ማንም ይፈጽመው ሕገ ወጥ ድርጊትን አናወግዛለን፤ እንቃወማለን፤ እናጋልጣለን:: የጥቅም ግንኙነት፣ የቤተሰብ ትስስር፣ ወይንም ለሥልጣን ቃል መገባባትም ሆነ ተስፋ ማሳደር ህገ ወጥ ድርጊትን አይተን እንዳላየን ለማለፍ፣ ሕገ ወጦችንም ከነጥፋታቸው ለማቀፍና ለመደገፍ አያስችለንም:: እኛም እንደ ብርቱከን ሕገ ወጥነትንና ማንአለብኝነትን አንለምደውም፤ አንተባበረውም:: «አንገት ከሚሰበር ባይበላስ ቢቀር» ነው ያለው ቴዲ አፍሮ!

ድጋፋችሁም ሆነ ተቃውሞአችሁ በእውነት መሰረት ላይ የቆመ ሳይሆን ተስፋ በምታደርጉት ሥልጣን ወይንም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ላይ የተንጠለጠለ መሆኑ ነው ህሊናዊ ዳኝነት ለመስጠት ያላስቻላችሁና የምትደግፉ የምትቃወሙትን ለመለየት ያቃታችሁ። ይህ ባይሆን «ክብርቱ‹ን የሚለየን የለም፤ ሞት አንኩዋን ቢሆን» ማለት ይዳዳችሁ የነበር ወህኒ በወረደች ማግስት ግልብጥ ብላችሁ አሰላለፋችሁን ለማስተ‹ከል አትደክሙም ነበር። ሰው በሚያስፈልጋት ወቅት የራስሽ ጉዳይ ብለው አሳልፈው ከሰጧት ጋር አትጣበቁም ነበር።

ምርጫ ቦርድ ኢ/ር ግዛቸው የአንድነት ሊቀመንበር ማለቱ ከምን የመነጨ ነው ተብሎ ሲጠየቅ ደጋፊ ሆናችሁ ልትሰለፉ ለምን? አንዴት? በማን? ተፈጸመ ብላችሁም ልትጠይቁ ሲገባ እነ ግዛቸውን ለመወንጀል ሲባል ብቻ የቀረበ ጽሁፍ አድርጋችሁ በማሰብ ባልተከራከራችሁ ነበር። ነገረ ሥራችሁ አያያዙን አይተህ ወደሚያደላው አይነት ነው። ነገ ደግሞ ከየትኛው ጎራ ከማንኛው ሰው ጋር አንደምትታዩ ጊዜ ያሳየናልና እድሜ መለመን ብቻ ነው። ለእውነት የሚቆም እንደ ገደል ላይ ዛፍ ሲወዛወዝ አይኖርም።

መል‹ም አዲስ ዓመት ይሆንላችሁ ዘንድ ምኞቴን የምገልጸው የድምጻዊ አብዱ ኪያርን « ምነው ሸዋ» የሚለውን ዘፈን ለአቶ ግርማና መሰሎቻቸው በመጋበዝ ነው። አዲሱ ዓመት እንደ ድምጻዊው ቲዎድሮስ ካሳሁን « ነፍሴ እጅ እንዳትሰጪው ለኪሴ » ለማለት የምንበቃበት ይሁን። አሜን!